# ዝም አልልም

ከበላይ መታፈሪያ (ዶ/ር)

በአገሬ ጉዳይ በኢትዮጵያ አልልም ዝም፣
በአገር ጠላት ወያኔ- በንዳ፣ አነግ-ተገንጣይ አልታለልም
በተገንጣይ- በባንዳ ልጆች አልጃጃልም፣
አገር ከፋፋይ ጽንፈኛ ቡድን አልቀበልም፣
በአታላይ ክህደት፣ በሃሰት ፍቅር አልካካስም።

በከሀዲ ውዥንብር አልደለልም፣
በአገሬ ጉዳይ ዝም አልልም፣
ያገባኛል በእጅጉ በታሪክም በእምነትም፣
በአማራ ማንነቴ በኢትዮጵያዊ ዜግነትም፣
በታሪክ ኩራት በቀደምት ትውልድ ነፃነትም፣
አቋሜ ነው ኢትዮጵያዊነት የማይገሰስ ምንጊዜም፣
የማይደፈር ፅናቴ፣ ብርቱ ነው ለድል ግብም፣
ፍንክች የማይል ለባንዳ-ተገንጣይ ለቅዥታም
አምርሬለሁ በፋኖነት አሻፈረኝ ዝም አልልም፣
በአገሬ ጉዳይ፣ለህዝብ ሰላም እንቅል አልተኛም
እምቢ ብያለሁ ለመብቴ፣ ዝም አልልም አልታለልም።

አውቀዋለሁ ጠላት ነው፣
አገርን ነው የተፈታተነው ፣
ሕዝብን ነው ያዋረደው፣
ታሪክን ነው ያራከሰው፣
ነፃነትን ነው የተሟገተው፣
ስንደቅ ዓላማችንን ነው ያመናጨቀው፣
አንድነታችንን ነው በንቀት ያየው፣
ኅብረታችንን ነው ሊበትን የሞከረው፣
ሰብዓዊ መብትን ነው ያሳጣው፣
ኢትዮጵያዊነትን ነው ያዳከመው፣

**እምቢ ብያለሁ አልደለልም**
**አሻፈረኝ ዝም አልልም**

አጀንዳው ይህ ነው አልዘናጋም፣
እምቢ ብያለሁ  ዝም አልልም፣
አውቀዋለሁ ወያኔን ፣  አነግንም በተገቢ፣
ኢህአዴግ ነው አስመሳይም አሳቢ፣
በስውር ፍቅር ግራ አጋቢ፣
በአብይ መደመር ይቅር ተመሩ፣
አጀንዳውን ለጥፋት ቀድሞው የሰሩ
ከመነሻው ከዚያው ጅምሩ፣
ለአገር ጥፋት ነው፣  ምስጥሩ
ኮሎኔል አብይ ለፖለቲካው ሽፋን  ምግባሩ፣
አጭበርባሪ ነው ተራ አምባገነን ተግባሩ
ከእንግዲህ በቃኝ አልታገስም፣
አመረርኩኝ ዝም አልልም፥
እፋለማለሁ ለህይወቴ፣ በአገር ወገን ድርድር የለም
የመጣው ይምጣ አልዘናጋም፣
**እምቢ ብያለሁ አልታለልም፣**
**አሻፈረኝ ! ዝም አልልም።**

**ህዝብ ከተቆጣ አንበሳ ነው ! ! !**

**ሲያነድም ነበልባል ነው ! ! !**

**ያላወቀ ያልቃል ! ! !**